


# ለአዲስ እንግዶቻችን መምሪያ

የዴንቨር የህዝብ ቤተ-መፅሀፍት ሁሉም የፈለገውን መማር፣ ማሠሥ፣ መፍጠር እንዲሁም አባል መሆን የሚችሉበት እንግዳ ተቀባይ ቦታ ነው:: በከተማችን ባሉት 26 ቅርንጫፎች ቤተ-መፅሀፍቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በማቅረብ ሰዎች እንዲቀራረቡ፣እንዲያድጉ እና እንዲያብቡ ማህበረሰብን ይገነባል:: ሁሉንም በነፃ::

## ማንም ሰው በቤተ-መፅሀፍቱ መገልገል ይችላል

እውነት ነው! በኮሎራዶ ያሉ ሁሉ የትውልድ ቦታችሁ የትም ይሁን ወይም የጊዜ ቆይታችሁ ሳይገድባችሁ የዴንቨር የህዝብ ቤተ-መፅሀፍትን ያለክፍያ መጠቀም ትችላላችሁ::

## በቤተ-መፅሀፍቱ ውስጥ ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ?

በቤተ-መፅሀፍቱ ውስጥ ብዙ ነገር ልታደርጉ ትችላላችሁ::
የሚከተለቱን ማድረግ ትችላላችሁ

- መፅሀፍትን፣ መፅሄቶችን፣ፊልሞችን እንዲሁም ሙዚቃ ተውሳችሁ ከ1-3 ሳምንት ቤታችሁ መውሰድ ትችላላችሁ::
- አብዛኞቹንም በኦንላይን ታገኟችኋላችሁ::
  ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር እና ኮፒ ማሽን መጠቀም ትችላላችሁ::
- መረጃ ለመፈለግ እንዲረዷችሁ የቤተ-መፅሀፍቱን ሰራተኞች መጠየቅ ትችላላችሁ::
- እንግሊዝኛ መማር::
- ለዜግነት ፈተናው ማጥናት::
- የማህበረሰብ አገልግሎቶች እንዲሁም የህዝብ የድጎማ ጥቅሞች ማግኘት::
- ስራ ለመፈለግ እገዛ ማግኘት::
- የንግድ ስራ ለመጀመር እገዛ ማግኘት::
- ለልጆች የሚሆኑ ነገሮችን እና የሚያዝናኑ ተግባራትን መፈለግ::
- የቤት ስራ ለመስራት እገዛ ማግኘት::
- ወደ ክፍል እና ወደ አዝናኝ ዝግጅቶች መጓዝ::
- የልብስ ስፌት መኪና፣ የድምፅ መቅጃ መሳሪያዎችን እንዲሁም የ3 ዲያሜንሽናል ፕሪንተሮችን መጠቀም ትችላላችሁ::

## የላይበራሪ ካርድ ያስፈልገኛል?

በፕላዛ ፕሮግራም ጉባኤ ማዕከላት፣ በተረት ጊዜ እና በኮምፒውተር ስልጠናዎች ወይም በአይዲያ ላብ ዝግጅቶች እና ፕሮግራሞች ለመሳተፍ የቤተ-መፅሀፍት ካርድ አያስፈልጋችሁም:: የቤተ-መፅሀፍት ካርዶች ነፃ ሲሆኑ ለመመዝገብም ቀላል ነው! የትኛውም ቦታ ካለ የዴንቨር የህዝብ ቤተ-መፅሀፍት ቅርንጫፍ ሲጎበኙ የእርሶ ፎቶ ያለው መታወቂያና የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ ይያዙ። የፎቶ መታወቂያው የየትኛውም ግዛት መታወቂያ፣ ወይም የየትኛውም ሀገር ፓስፖርት፣ ወይም የቆንስላ መታወቂያ መሆን ይችላል::

DENVER PUBLIC LIBRARY



## በካርዳችሁ ከቤተ-መፅሀፍቱ መዋስ የምትችሏቸው ነገሮች

- መፅሀፍት እና ኤሌክትሮኒክ መፅሀፍት::
- የድምፅ ቅጂ መፅሀፍት እና የድምፅ ቅጂ ኤሌክትሮኒክ መፅሀፍት::
- ፊልሞች (በዲቪዲ፣ ብሉሬይ እና ቀጥታ በኦንላይን)::
- ሙዚቃ (በሲዲ እና ቀጥታ በኦንላይን)::
- ማጋዚኖች እና የዲጂታል ጋዜጦችን::
- የዋይ-ፋይ ሆትስፖት::
- ለቤተ-መዘክር እና የስቴት ፓርኮች መግቢያ::
- እንዲሁም ለብዙ ብዙ ነገሮች!

## ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

በፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እንዲሁም በ26ቱም የዴንቨር የህዝብ ቤተ-መፅሀፍቶች ዙሪያ መረጃ ለማግኘት የቤተ-መፅሀፍቱን ድረገፅ denverlibrary.org ይጎብኙ::

**የፕላዛ ፕሮግራም**
የፕላዛ ጉባኤ ፕሮግራም ማዕከላት ከመላው ዓለም የተሰበሰቡ ፍልሰተኞች ከአዳዲስ ሰዎች እና መረጃዎች ጋር የሚገናኙበት ክፍት የማህበረሰብ ዝግጅቶች ማዕከል ነው:: በዚያ የሚደረጉ ተግባራትም፤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልምምድ፣ የዜግነት ፈተና ዝግጅት፣ የኮምፒውተር ትምህርት፣ የስነ ጥበብ እና የዕደ ጥበብ ተግባራት እንዲሁም የማህበረሰብ ግንባታ እና ሌሎች ተግባራት ናቸው::

**የማህበረሰብ አገልግሎቶች**
ከማህበረሰብ አገልግሎት ልዩ ባለሙያ ጋር በመገናኘት እንደ መጠለያ፣ የመኖሪያ ቤት፣ ምግብ፣ የህዝብ ድጎማ፣ የአዕምሮ ጤና፣ የጤና ህክምና፣ የሱስ ማገገሚያ ህክምና እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶች እንድታውቁና ድጋፍ እንድታገኙ ያስችላችኋል::

**የተረት ጊዜ**
ታሪኮች፣ ዘፈኖች፣ መዝሙሮች እንዲሁም ሌሎች፤ለህፃናት፣ ለለጋ ልጆች እንዲሁም ወላጆች ወይም ሞግዚቶች በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽኛ ይቀርባል::

**የኮምፒውተር ስልጠናዎች**
በቴክኖሎጂ ዙሪያ በሰፊው ከመሰረታዊ እስከ ልህቀት ደረጃ፤ በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽኛ ቋንቋ ስልጠና እና የግል ልምምዶች ይቀርባሉ::

**የአይዲያ ላቦች**
ይህ የፈጠራ ቤተ-ሙከራ ቦታው ለማህረሰቡ ነፃ የመፍጠሪያ ክፍት ቦታ ነው:: የቤተ-መፅሀፍቱ  አይዲያ ላብ ማንም ሰው ድረገፆች፣ ቪዲዮች፣ ጌሞች፣ ሙዚቃና ሌሎችን ነገሮች መፍጠር የሚችልበት ቦታ ነው:: ምንም እንኳ ያሉት መሳሪያዎች በየቦታው የተለያዩ ቢሆኑም በተለየ ደግሞ በሮዶልፎ “ኮሪኪ” ጎንዛሌዝ ቅርንጫፍ የሚገኘው ቤተ-መፅሀፍት የአይዲያ ላቡ ትኩረት ያደረገው በቴክስታይል ዙሪያ፤ በልብስ ስፌት መኪና እና በሽመና እቃ ሲሆን ሰወች የፈለጉትን ነገር፤ ልብስ፣ ጥልፍና ጥለት ወዘተ መስራት የሚችሉበት ዝግጅት ነው:: በአይዲያ ላቦች ውስጥ የአይዲያ ቤተ-ሙከራዎች በውስብስብ መሳሪያዎች እና በቴክኒካል ሰራተኞች ድጋፍ የተዋቀሩ ሲሆኑ፤ በቀላሉ ልታሳኳቸው እና በነፃ ልታስቧቸው የማይቻላችሁን ነገሮችን እንድታደርጉ ያስችሏችኋል:: የቤተ-መፅሀፍት ካርድ አያስፈልጋችሁም::

## የምንጠቀማቸው ቃላት

- borrow or check out: ለተወሰነ ጊዜ ወደ ቤት መውሰድ::
- due date: የወሰዳችሁት እቃ ወደ ቤተ-መፅሀፍቱ የሚመለስበት ቀን::
- items or materials: መፅሀፍት፣ ፊልሞች፣ ሙዚቃ፣ወይም ሌሎች ነገሮች የቤተ- መፅሀፍቱ ንብረት ሆነው ለእናንተ መገልገያነት የተዘጋጁ::
- Librarian፡ ቤተ-መፅሀፍቱን እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ እና የምትፈልጉትን መረጃ ለማግኘት የሚረዷችሁ ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች::
- library card: ከቤተ-መፅሀፍቱ እቃ ለመዋስ የሚያስፈልጋችሁ ነፃ የአባልነት ካርድ::
- photo ID: ስማችሁ እና ፎቷችሁን የያዘ የመታወቂያ ካርድ:: የየትኛውም ግዛት መታወቂያ፣ የየትኛውም ሀገር ፓስፖርት፣ ወይም ቆንስላ መታወቂያ መሆን ይችላል:: ያላችሁን ነገሮች ይዛችሁ ኑ እና እኛ የቤተ-መፅሀፍት ካርድ እንዲኖራችሁ ከእናንተ ጋር እንተባበራለን::
- proof of address: የምትኖሩበትን ቦታ የሚያረጋግጥ ስማችሁ ያለበት ቢል ወይም ሌላ መልዕክት የያዘ ወረቀት::
- receipt: ምን አይነት እቃ እንደተዋሳችሁ እና መቼ እንደሚመለስ የተፃፈበት ደረሰኝ::
- renew: የተዋሳችሁትን እቃ ቆይታ ማራዘም::
- return: የወሰዳችሁትን እቃ ለቤተ-መፅሀፍቱ መመለስ::